ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን ሰኔ 01 2000 ዓ.ም

# አፋኙ ስርዓት ሌላ የዲፕሎማሲ ኪሳራ ገጠመው

ካናዳ አምባሳደሯን ወደአገሯ በመጠራቷ አባገነኑ የመለስ ዜናዊ ስርዓት ሰሞኑን ሌላ የዲፕሎማሲ ኪሳራ እንደገጠመው የዜና ምንጩች ገለጡ ። እንደ ምንጩቹ ገለጣ ለአምባሳደሩ መጠራት ምክንያት የሆነዉ የካናዳ ዜግነት ያለዉን የሱማለያ ተወላጅ ሙክታር የተባለዉን ግለሰብ ወራሪዉ የመለስ ዜናዊ ጦር ከ16 ወራት በፊት ሞቋዲሾን በተቆጣጠረበት ሰአት ካሠረዉ ቦኋላ እርሱን ለማስፈታት በተደረገው ጥረት የወያኔ መንግሥት በያዘው ግተር አቋም መሆኑ ታውቆአል።

በአሸባሪነት ተጠርጥሮ አዲስ አበባ ውስጥ ባልታወቀ ቦታ በልዩ እሥር ላይ የሚገኘው ሙክታር በጀነቫ ኮንቬንሽን መሰረት ሊያገኝ የሚገባውን በሃገሩ ኮንሱላር የመጎብኘት መብት መነፈጉ ለውዝግቡ መፈጠር ምክንያት ሆኖአል። የካንዳ የብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከሁለት ቀን በፊት እንደገለፀው ከሆን የካናዳ ፓርላማ ጸሃፊ አዲስ አበባ ድረስ በመጓዝ ለጉዳዩ እልባት ለመስጠት ያደረጉት ጥረት ሳይሳካ ቀርቷል ። ይህ ጉዳይ በተቃዋሚው የሊብራል ፓርቲ በኩል ትልቅ የመወይይ አጀንዳ በማስነሳቱ በጠቅላይ ሚኒስት ሃርፐር መንግስት ላይ በፈጠረው ከፍተኛ ግፊት አምባሳደሩን እስከማስጠራት ደርሶአል።

እንደሚታወስው እስታሊናዊው የመለስ ዜናዊ ስርዓት በቅርቡ ከኖርዎይ ጋር የኤርትራን መንግስት ትረዳልች በሚል ፣ ከካታር ደግሞ በምስራቅ አፍሪካ ያሉ አሸባሪውችን እና የኤርትራን መንግስት ትረዳለች በሚል ሰበብ የዲፕሎማሲያዊ ገንኙነቶችን አቋርጧል

ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱም ሐገሮች በነዳጅ ሃብታቸው የሚታውቁ በመሆናቸው በተለይ የነዳጅ ዋጋ 139 ዶላር በደረሰበት በአሁኑ ሰዓት የበለጠ አስፈላጊዎች ናቸው ።

ከ60 ሽህ በላይ ኢትዮጵያውያን ሰደተኞችን የሚኖሩባት ካናዳ በየአመቱ ወደ 120 ሚሊዮን ዶላር የሚጠጋ እርዳታ እንድምትለግስ ይታወቋል።